Temari.et

# Civics and Ethical Education, 2012 EC, Grade 8 model exam

Grade 8 · Citizenship Education · 2012 E.C.

**MARKING KEY: CONFIDENTIAL**

**Time allowed:** 120 minutes | **Questions:** 55 | **Total marks:** 55

Sit this paper online with instant scoring, free on Temari.et.
temari.et/exam-prep/papers/grade-8-civics-2012-model

**1.** ከሚከተሉት ዲሞክራሲያዊ መርህ ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

A. የህግ የበላይነት መርህ
B. የግልፅነትና የተጠያቂነት መርህ
C. ✓ **የአናሳዎች ድምፅ የበላይነት**
D. የብዙሃን ድምፅ መከበር

**Answer:** C
ዲሞክራሲ የሚመራው በብዙሃን ድምፅ የበላይነት እና በአናሳዎች መብት መከበር መርህ እንጂ 'የአናሳዎች ድምፅ የበላይነት' በሚል መርህ አይደለም።

**2.** ከሚከተሉት መካከል ዲሞክራሲያዊ መብት የሆነው የቱ ነው? (1)

A. በመረጡት አከባበር መኖር
B. ✓ **ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ**
C. በመረጡት ስራ ዘርፍ መስራት
D. በህይወት የመኖር መብት

**Answer:** B
በኢፌዴሪ ህገ-መንግስት መሰረት ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ መብት (አንቀጽ 30) በዲሞክራሲያዊ መብቶች ስር የተመደበ ሲሆን በህይወት የመኖር መብት ግን በሰብአዊ መብቶች ስር ይመደባል።

**3.** ስልጣን በማዕከል ብቻ ተይዞ የሚመሰረት የመንግስት ስያሜ ምን ይባላል? (1)

A. ፌደራላዊ
B. ✓ **አሀዳዊ**
C. ኮንፌዴሬሽን
D. ዲሞክራሲያዊ

**Answer:** B
የመንግስት የስልጣን እርከኖች በሙሉ በአንድ ማዕከል ብቻ ተከማችተው የሚገኙበት የመንግስት መዋቅር አሀዳዊ (Unitary) መንግስት ይባላል።

**4.** የሃሳብ ልዩነት በሚከስትበት ወቅት ጥሩ የመግባባት መንፈስ የሚፈጥሩ ሁኔታዎች ከሚከተሉት የትኞቹ ናቸው? (1)

A. አለመቻቻል ፣ ውይይት፣ መደማመጥ
B. ✓ **ውይይት፣ መደማመጥ፣መቻቻል**
C. አለመደማመጥ፣ መቻቻል፣ውይይት
D. አለመወያየት፣ መቻቻል፣ አለመደማመጥ

**Answer:** B
የሃሳብ ልዩነቶች በሚፈጠሩበት ወቅት ሰላማዊ መግባባትን ለመፍጠር ግልፅ ውይይት ማድረግ፣ እርስ በእርስ መደማመጥ እና የሌሎችን ሃሳብ መቻቻል ወሳኝ ናቸው።

**5.** ከሚከተሉት በፌዴራልና በክልል የመንግስታት አወቃቀር ስርዓት ውስጥ የሚመደቡ የስልጣን አካላት የትኞቹ ናቸው? (1)

A. ✓ **ህግ አውጪ፣ህግ አስፈፃሚ፣ህግ ተርጓሚ**
B. የህግ መወሰኛ፣ የህግ መምሪያ፣ ህግ ተርጓሚ
C. የህግ ተርጓሚና የህግ መምሪያ
D. ህግ አውጪና ህግ አስፈፃሚ

**Answer:** A
በዲሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ በመንግስት መዋቅር የሚገኙት ሦስቱ የስልጣን አካላት ህግ አውጪ፣ ህግ አስፈፃሚ እና ህግ ተርጓሚ ናቸው።

**6.** የህዝብ አገልጋይ ባለስልጣናት ሊላበሱት የሚገባቸው የመልካም ስነ-ምግባር መገለጫ የቱ ነው? (1)

A. አድሎ መፈፀም
B. ስልጣንን በአግባቡ አለመጠቀም
C. ✓ **ለህዝብ ጥያቄ መልስ መስጠት**
D. ለህግ አለመገዛት

**Answer:** C
የህዝብ አገልጋይ የሆኑ ባለስልጣናት ተጠያቂነትንና ግልፅነትን በማስፈን የህዝብን ጥያቄዎችና ፍላጎቶች በአግባቡ ማስተናገድ እና ምላሽ መስጠት አለባቸው።

**7.** በሰዎች መካከል በቃልኪዳን ተጠብቆ የሚያዝ ድርጊት የሆነው የቱ ነው? (1)

A. መልካም ስነ-ምግባር
B. ታማኝነት
C. ✓ **ሚስጢር**
D. ወዳጅነት

**Answer:** C
በስነ-ምግባር ትምህርት መሰረት 'ሚስጢር' በሰዎች መካከል በቃልኪዳንና በእምነት ተጠብቆ የሚያዝ መረጃ ወይም ድርጊት ነው።

**8.** ከሚከተሉት የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብት መከበሩን የሚገልፀው ሃሳብ የቱ ነው? (1)

A. ✓ **በራሳቸው ቋንቋ መጠቀም**
B. ባህላቸውን እንዳይገልፁ ማድረግ
C. እራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስታድሩ ማድረግ
D. ታሪካቸውን እንዳይንከባከቡ ማስቻል

**Answer:** A
የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች የእኩልነት መብት መከበር አንዱ መገለጫ ቋንቋቸውን የመጠቀም፣ የማሳደግና የመፃፍ መብት (አንቀጽ 39) መረጋገጡ ነው።

**9.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ- መንግሰስት ድንጋጌ መሰረት የሴቶች የእኩልነት መብት መካከል የማይካተተው የትኛው ነው? (1)

A. ለእኩል ስራ እኩል ክፍያ ማግኘት
B. ንብረት ማፍራት
C. ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊት ነፃ መሆን
D. ✓ **ጋብቻን በቤተሰቦቿ ፍላጎት መመስረት**

**Answer:** D
በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 34 እና 35 መሰረት ጋብቻ በሁለቱም ተጋቢዎች ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ የሚመሰረት እንጂ በቤተሰብ ፍላጎትና ግፊት የሚደረግ አይደለም።

**10.** የአካል ጉዳተኞች የእኩልነት መብት ሲከበር ለሀገር የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ ምንድነው ? (1)

A. በልመና ተግባር ላይ መሰማራት
B. ምፅዋትን መጠየቅ
C. ከጥገኝነት አስተሳሰብ አለመላቀቅ
D. ✓ **አቅማቸውን ሙሉ በሙሉ በመጠቀም በልማት መሳተፍ**

**Answer:** D
የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል እና መብት ሲከበርላቸው እምቅ አቅማቸውን ተጠቅመው በሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ውስጥ ሙሉ በሙሉ መሳተፍ ይችላሉ።

**11.** ፍትሀዊነት ምን ሊገልፅ ይችላል ? (1)

A. ፍርድን ማጣመም
B. ✓ **በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ልዩነትን አላግባብ እንዳይፈጠር መከላከል**
C. ማንኛውም አይነት ልዩነት አለማስተናገድ
D. ሚዛናዊነትን ያልጠበቀ መሆን

**Answer:** B
ፍትሐዊነት (justice/fairness) ማለት በሰዎች መካከል ተገቢ ያልሆነ ወይም አላስፈላጊ ልዩነት እንዳይኖር እና እኩል አያያዝ እንዲሰፍን ማድረግ ነው።

**12.** ዜጎች ባላቸው የሀብት ይዘታ ነግደው ባገኙት የትርፍ መጠን ተገናዝቦ የሚተመንበት ስርዓት ምንድነው? (1)

A. መዋጮ
B. ✓ **ግብር**
C. ወለድ
D. የመጠባበቂያ በጀት

**Answer:** B
ግብር (tax) ዜጎች ባላቸው ሀብትና በሚያገኙት ገቢ ወይም ትርፍ መጠን ተሰልቶ ለመንግስት አገልግሎቶች ማስፈጸሚያ የሚከፈል ህጋዊ ክፍያ ነው።

**13.** የሀገርን ገፅታ ከሚጎዱ አፍራሽ ተግባራት መካከል አንዱ የቱ ነው ? (1)

A. ሙስናና የኮንትሮባንድ ንግድ መጥፋት
B. ለጥቅም ሲባል ዕውነታን አዛብቶ ለህዝብ አለማቅረብ
C. ግብርን በወቅቱ መክፈል
D. ✓ **የእርስ በርዕስ ጦርነት**

> **Answer:** D
> የእርስ በእርስ ጦርነት የዜጎችን ህይወት የሚያጠፋ፣ ንብረት የሚያወድም እና የሀገርን ገጽታ በእጅጉ የሚያበላሽ አፍራሽ ተግባር ነው።

**14.** ህጋዊ ወይም ህሊናዊ ተጠያነት ያለው ጽንስ ሀሳብ ሆነው የትኛው ነው? (1)

A. የህዝብ ሉአላዊነት
B. ጠንካራ የስራ ባህል
C. ✓ **የሃላፊነት ስሜት**
D. ቃልኪዳን

> **Answer:** C
> ኃላፊነት (responsibility) አንድ ሰው የሚጠበቅበትን ተግባር የማከናወን ህጋዊ ወይም ህሊናዊ ግዴታና ተጠያቂነት ነው።

**15.** የጋራ ሃላፊነትን የመወጣት ጥቅም ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

A. ብዙ ሰዎችን ተጠቃሚ ያደርጋል
B. ስራን ያቀላጥፋል
C. ✓ **በሰዎች መካከል ግጭት ይፈጥራል**
D. ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎን ያሳድጋል

> **Answer:** C
> የጋራ ኃላፊነትን በአግባቡ መወጣት ህዝባዊ ትብብርን ያጠናክራል እንጂ በሰዎች መካከል ግጭት አይፈጥርም።

**16.** ለሀገር ልማትና ለኢኮኖሚ እድገት እንቅፋት ያልሆነው የቱ ነው? (1)

A. ጥገኝነትን አምኖ መቀበል
B. ሳይሰሩ መኖርን አለመፀየፍ
C. ✓ **ጠንካራ የስራ ባልን ማዳበር**
D. ልመናና እንደገቢ ምንጭ መቁጠር

> **Answer:** C
> ጠንካራ የስራ ባህልን ማዳበር ለሀገር እድገትና ብልጽግና ወሳኝ አንቀሳቃሽ ኃይል እንጂ እንቅፋት አይደለም።

**17.** ራስን መቻል ከሚለው ፅንስ ሀሳብ ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ? (1)

A. የራስን ጠንካራና ደካማ ጎን ማወቅ
B. የምንሰራውን ስራ በራስ አቅምና ችሎታ መስራት
C. የራስን አቅምና ችሎታ ለይቶ ማወቅ
D. ✓ **የጠባቂነት ስሜትን ማዳበር**

> **Answer:** D
> ራስን መቻል (self-reliance) የጠባቂነት ስሜትን ማጥፋት እንጂ የጠባቂነት ስሜትን ማዳበርን አያካትትም።

**18.** ከማንኛውም የፖለቲካ ፣ ወታደራዊ እና ሐይማኖታዊ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የሚቋቋም ማህበር የቱ ነው ? (1)

A. ✓ **የሲቪክ ማህበር**
B. ወታደራዊ ማህበር
C. የፖለቲካዊ ማህበር
D. ሐይማኖታዊ ማህበር

> **Answer:** A
> የሲቪክ ማህበራት (civic associations) ከመንግስታዊ፣ ከፖለቲካዊ፣ ከወታደራዊ እና ከሃይማኖታዊ ተጽዕኖዎች ነፃ ሆነው የሚቋቋሙ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ህዝባዊ አደረጃጀቶች ናቸው።

**19.** የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት የልማት ዓላማዎችን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው ? (1)

A. ሁሉንም ዜጎች ተጠቃሚ ማድረግ
B. ✓ **የጥቂት ግለሰቦችን ኢኮኖሚ ማሳደግ**
C. ፈጣን ኢኮኖሚ እድገት ማምጣት
D. የህዝብን ፍላጎት ማሟላት

> **Answer:** B
> በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 89 መሰረት የመንግስት የልማት ዓላማ ሁሉንም ዜጎች በእኩልነት ተጠቃሚ ማድረግ እንጂ የጥቂት ግለሰቦችን ሀብት ማካበት አይደለም።

**20.** በኢ.ፊ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት አንቀፅ 11 ተደነገገው (1)

A. ሐይማኖታዊ መንግስት መመስረት
B. መንግስት በሐይማኖት ጉዳይ ጣልቃ ይገባል
C. ✓ **መንግስትና ሐይማኖት የተነጣጠሉ ናቸው**
D. ሐይማኖት በመንግስት ጉዳይ ላይ ጣልቃ ይገባል

**Answer:** C
በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ-መንግስት አንቀፅ 11 መሰረት መንግስትና ሃይማኖት የተለያዩ መሆናቸውና አንዱ በሌላው ጣልቃ እንደማይገባ ተደንግጓል።

**21.** ከዜጎች ባህሪያት ውስጥ ለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ አስተዋፅኦ የሌለው የቱ ነው ? (1)

A. ✓ **ግለኝነት**
B. ተግባራዊነት
C. ፍቃደኝነት
D. ተነሳሽነት

**Answer:** A
ግለኝነት የራስን ጥቅም ብቻ ማዕከል በማድረግ የህብረተሰብ ጉዳይ እንዳይመለከተን ስለሚያደርግ ለንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ አጋዥ ሳይሆን እንቅፋት ነው።

**22.** ኤች.አይ.ቪ ኤድስ በሀገራችን የትኛውን ህብረተሰብ ክፍል በይበልጥ ያጠቃል? (1)

A. ሕፃናትን
B. ✓ **ወጣቶችን**
C. አዛውንትን
D. አረጋውያንን

**Answer:** B
ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሀገራችን በይበልጥ የሚያጠቃው አምራችና ንቁ የሆነውን የወጣቱን የህብረተሰብ ክፍል ነው።

**23.** በራስ የመተማመን ስሜትን ለማዳበር ከሚረዱ ሁኔታዎች መካከል አንዱ የቱ ነው? (1)

A. የራስ ችሎታን ያለማወቅና ያለማበልፀግ
B. የሌላውን ሀሳብ ያለማክበር
C. ✓ **እውነታን በፅናት መቀበል**
D. እቅድን ያለማውጣትና ስራን ያለመገምገም

**Answer:** C
ያሉ ተጨባጭ እውነታዎችን በፅናትና በድፍረት ተቀብሎ ችግሮችን ለመፍታት መሞከር ራስን የመተማመን ስሜትን ያዳብራል።

**24.** ከሚከተሉት ለቅርሶች መበላሸት መንስኤ ከሆኑት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው? (1)

A. የእሳት ቃጠሎና ጦርነት
B. ✓ **እድሳትና እንክብካቤ ማድረግ**
C. የትምህርት እጦት
D. አስከፊ ድህነት

**Answer:** B
ቅርሶችን ማደስና መንከባከብ ለህልውናቸውና ለደህንነታቸው የሚደረግ ጥበቃ እንጂ ለመበላሸታቸው መንስኤ አይደለም።

**25.** ከሚከተሉት ከአውቀት፣ ከኢኮኖሚ እና ከማህበራዊ ጥገኝነት ተላቆ ነፃ መሆንን የሚያመለክት ፅንሰ ሀሳብ የቱ ነው (1)

A. ✓ **ራስን መቻል**
B. ንቁ ህዝባዊ ተሳትፎ
C. የቁጠባ ባህል
D. በራስ መተማመን

**Answer:** A
ራስን መቻል (self-reliance) ማለት ከኢኮኖሚ፣ ከማህበራዊና ከእውቀት ጥገኝነት ነፃ ሆኖ በራስ አቅም መቆምን የሚያሳይ ፅንሰ-ሀሳብ ነው።

**26.** ቁጠባ ማለት ምን ማለት ነው ? (1)

A. ዛሬን እየተቸገሩ ለነገ ማስቀመጥ ነው
B. ✓ **ከዕለት ፍጆታ ላይ ቀንሶ ማስቀመጥ ነው**
C. በስራ የተገኘውን ገቢ በሙሉ መጠቀም ነው
D. በስራ የተገኘውን ገቢ በሙሉ ማስቀመጥ ነው

**Answer:** B
ቁጠባ ማለት ከዕለት ፍጆታና ከወቅታዊ ወጪ ተራፊ የሆነን ሀብት ወይም ገንዘብ ለወደፊት ጥቅም በማሰብ ማስቀመጥ ነው።

**27.** ከሚከተሉት የእውቀት አገልግት ውስጥ የማይካተተው የቱ ነው ? (1)

A. ለምርምር አገልግሎት
B. ለፈጠራ ሥራ ይጠቅማል
C. ✓ **በዜጎች መካከል የሃሳብ ልዩነት ይፈጥራ**
D. ለሀገር እድገት ወሳኝ ይሆናል

> **Answer:** C
> እውቀት ለፈጠራ፣ ለምርምርና ለሀገር እድገት የሚውል እንጂ በዜጎች መካከል አለመግባባትንና ጎጂ ልዩነትን ለመፍጠር የሚያገለግል አይደለም።

**28.** ኋላቀር አስተሳሰብን ለማስወገድ ከሚያግዙ ሁኔታዎች የሚመደበው የቱ ነው ? (1)

A. ጎታች አመለካከቶችን ማራመድ
B. በስሜት ላይ የተመረኮዘ አስተያየት መስጠት
C. በጭፍን አመለካከቶች መመራት
D. ✓ **በእውቀትና በምክንያታዊ የተደገፈ መሆን**

> **Answer:** D
> ኋላቀር አስተሳሰብንና ጎጂ ልማዶችን ለማስወገድ ውሳኔዎችን በእውቀትና በምክንያታዊ አስተሳሰብ ላይ መመስረት ወሳኝ ነው።

**29.** ከሚከተሉት መርህ ውስጥ የዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚቆምበት ምሰሶ የቱ ነው ? (1)

A. ነፃ የፖለቲካ ስልጣን ውድድር
B. ✓ **የህግ የበላይነት**
C. ግልፅነትና ተጠያቂነት
D. የብዙሃኑ ድምጽ የበላይነትና አነስተኛው መከበር

> **Answer:** B
> በስነ-ዜጋና ስነ-ምግባር ትምህርት ውስጥ የህግ የበላይነት የማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ዋነኛ ምሰሶና መሰረት እንደሆነ ተደንግጓል።

**30.** ከግለሰብ ሰብአዊ መብቶች መካከል የሚመደበው የቱ ነው? (1)

A. የእኩልነት መብት
B. የሐይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት
C. ✓ **በአካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብት**
D. የመዘዋወር ነፃነት

> **Answer:** C
> Under the FDRE Constitution, Chapter 3 is divided into Human Rights and Democratic Rights. Article 16, which guarantees the right to the security of person (በአካል ላይ ጉዳት እንዳይደርስ የመጠበቅ መብት), is classified under Human Rights, while equality, freedom of religion, and freedom of movement are categorized as Democratic Rights.

**31.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ህግ አስፈፃሚ አካል ማን ነው? (1)

A. ✓ **የሚኒስትሮች ምክር ቤት**
B. ጠቅላይ ፍርድ ቤት
C. የተወካዮች ምክር ቤት
D. የክልል መስተዳድር

> **Answer:** A
> According to the FDRE Constitution, the highest executive power of the Federal Government is vested in the Prime Minister and the Council of Ministers (የሚኒስትሮች ምክር ቤት).

**32.** ከቡድን ዲሞክራሲያዊ መብቶች መካከል የማይመደበው የቱ ነው? (1)

A. የህዝብ ሉአላዊነት
B. የመደራጀት መብት
C. ✓ **በህይወት የመኖር መብት**
D. የመሰብሰብ መብት

> **Answer:** C
> The right to life (በህይወት የመኖር መብት) is a fundamental individual human right, whereas popular sovereignty, freedom of association, and assembly are collective or group democratic rights.

**33.** በመንግስት ባለስልጣናት ላይ የስልጣን ገደብ መጣል ያስፈለገው (1)

A. ✓ **ህብረተሰቡ ተገቢ አገልግሎት እንዲያገኝ**
B. አድሎአዊ አሰራሮችንና ህገወጥነትን ለማበረታታት
C. የዜጎችን ሰበዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ለመጣስ
D. ባለስልጣናት በስልጣናቸው እንደፈለጉ እንዲጠቀሙ ለማድረግ

> **Answer:** A
> Constitutional limits on government power are established to prevent the abuse of authority and ensure that citizens receive proper, lawful, and equitable service.

**34.** በዜጎች መካከል ልዩነት ሳይደረግ ለህይወታቸው ለንብረታቸው ህጋዊ ጥበቃ ዋስትና መስጠት ማለት ነው (1)

A. የስልጣን ገደብ
B. ፍትህዊነት
C. ✓ **የህግ ከለላ**
D. ሀቀኝነት

**Answer:** C
Legal protection (የህግ ከለላ) refers to guaranteeing legal security and protection to the lives and properties of all citizens without discrimination.

**35.** የበጀት ጉድለትን ለማተካከል የሚደረግ የገንዘብ ድጋፍ ሆነው የቱ ነው? (1)

A. ✓ **ድጎማ**
B. ግብር
C. ጉቦ
D. ቁጠባ

**Answer:** A
A subsidy or grant (ድጎማ) is financial assistance provided by the government to offset budgetary deficits or support public services.

**36.** ለሀገር ልማት አፈፃፀም ውጤታማነት መንግስት የሚያወጣው ህግ፣ የሚደነግገው ደንብና መመሪያ (1)

A. ህገ-መንግስት
B. አዋጅ
C. ዕቅድ
D. ✓ **ፖሊስና እስትራቴጂ**

**Answer:** D
In Ethiopian civics education, policies and strategies (ፖሊሲና ስትራቴጂ) are defined as the guiding frameworks, rules, and regulations formulated by the government to achieve national development goals.

**37.** ኤች.አይ.ቪ ኤድስን በአስተማማኝ የመከላከያ ዘዴ የሆነው የቱ ነው? (1)

A. ኮንዶም መጠቀም
B. በአንድ መወሰን
C. ✓ **ከጋብቻ በፊት ወሲብ አለመፈፀም**
D. የደም ንክኪን ማስወገድ

**Answer:** C
In civic and health education curricula, abstinence from sexual intercourse before marriage is taught as the most reliable and 100% effective method of preventing the sexual transmission of HIV/AIDS.

**38.** ሰዎች ሙስና እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው ነገር ምን ሊሆን ይችላል? (1)

A. የተሻለ ደመወዝ ማግኘታቸው
B. ፍላጎታቸው ሲሟላላቸው
C. ስልጣናቸው ሲገደብ
D. ✓ **ሀላፊነት ሲጎድላቸው**

**Answer:** D
A lack of civic responsibility, accountability, and ethical integrity is a primary internal factor that leads individuals to engage in corrupt practices.

**39.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት ህግና ደንብ ማውጣትና ማፅደቅ የማን ስልጣን ነው? (1)

A. ✓ **የተወካዮች ምክር ቤት**
B. የፌዴሬሽን ምክር ቤት
C. የሚኒስትሮች ምክር ቤት
D. የዳኞች ጉባኤ

**Answer:** A
According to Article 55 of the FDRE Constitution, the House of Peoples' Representatives (የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት) holds the highest legislative power to enact and approve federal laws.

**40.** ከሚከተሉት መካከል የፌዴራልና የክልል መንግስታት አንድነትን የሚያሳየው (1)

A. ✓ **የስልጣን አወቃቀራቸው ተመሳሳይ መሆኑ**
B. አዲስ አበባን በጋራ ማስተዳደር
C. ገንዘብና መከላከያ ሰራዊትን በጋራ መስተዳደር
D. በሁለቱም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መኖር

> **Answer:** A
> Both the federal government and regional state governments in Ethiopia share a similar structure of power, each being divided into legislative, executive, and judicial branches.

**41.** የፌዴራል የመንግስት አስተዳደር ከሌሎች የመንግስት አስተዳደሮች የሚለየው ዋነኛ ባህሪው የትኛው ነው? (1)

A. ሥርዓቱ በህግ የበላይነት የሚመራ ነው
B. ✓ **በፌዴራል መንግስት እና በክልል መንግስታት መካከል የሚኖር የስልጣን ክፍፍል**
C. የተጠያቂነት ሥርዓት መኖር
D. ፕሬዝዳንታዊ መንግስት አስተዳደር መኖር

> **Answer:** B
> The fundamental defining characteristic that distinguishes a federal system from unitary and other forms of government is the constitutionally entrenched division of power between the central federal government and regional states.

**42.** የኢትዮጲያ የውጪ ግንኙነት ፖሊሲ ምንን መሰረት ያደረገ ነው? (1)

A. ✓ **የህዝብን ጥቅም ማስቀደም**
B. የባለስልጣናትን ፍላጎት መሰረት ማድረግ
C. ኢኮኖሚን ብቻ መሰረት ማድረግ
D. ላደጉት ሀገራት መንግስት መቆምን

> **Answer:** A
> Article 86 of the FDRE Constitution stipulates that Ethiopia's foreign relations policy is primarily guided by safeguarding national sovereignty and prioritizing the interests and well-being of its citizens.

**43.** ህገ መንግስት ምንድን ነው? (1)

A. የወንጀለኛ መቅጫ ህጎችን የያዘ ነው
B. ሰበአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ብቻ የያዘ ህግ ነው
C. የመንግስትን ታሪክ የሚያብራራ ሰነድ ነው
D. ✓ **የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ ነው**

> **Answer:** D
> A constitution is the supreme law of the land (የህጎች ሁሉ የበላይ ህግ); any other law, customary practice, or government decision that conflicts with it is invalid.

**44.** ዕውቀትን ለማዳበር በተጨባጭ የሚረዳው (1)

A. የስራ ዕቅድ
B. ህልም
C. በስራ የማይተረጎም ምኞት
D. ✓ **የተሰበሰቡ መረጃዎች**

> **Answer:** D
> Knowledge is systematically built and developed upon the empirical gathering, analysis, and interpretation of collected data and factual information.

**45.** አካል ጉዳተኞችን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው? (1)

A. አካል ጉዳተኞች ማንኛውም ሰው ያለውን ግዴታ እና መብት አሏቸው
B. ✓ **አካል ጉዳተኞች መብት አንጂ አገራዊ ግዴታ የለባቸውም**
C. የአካል ጉዳተኞች መብት እንዲከበር ሁሉም ዜጋ ሀላፊነት አለባቸው
D. አካል ጉዳተኞች ለሀገር የሚጠቅም ተግባር ማከናወን ይችላሉ

> **Answer:** B
> The statement that persons with disabilities have only rights and no national duties is incorrect; like all citizens, they have both constitutional rights and civic responsibilities according to their capabilities.

**46.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት መሰረት አንድ ሰው ወንጀለኛ ነው የሚባለው እንዴት ነው ? (1)

A. ፖሊስ ክትትል ሲያደርግበት
B. ፖሊስ በጥርጣሬ ሲይዘው
C. ✓ **እጅ ከፍንጅ ሲያዝ ወይም በምስክሮች ሲረጋገጥ**
D. ፖሊስ በቁጥጥር ስር ሲያውለው

**Answer:** C
Under constitutional due process and the presumption of innocence, an individual cannot be regarded as a criminal merely by police suspicion or arrest; their guilt must be substantiated by evidence, witness testimony, or being caught in flagrante delicto.

**47.** ሙስናን ለማስወገድ የኢትዮጲያ መንግስት እና ህዝብ በዋነኝነት ማድረግ ያለባቸው (1)

A. የፀረ ሙስና ኮሚሽንን ማጠናከር
B. ✓ **የአመለካከት ለውጥ ለማምጣት መስራት**
C. ድህነትን ማጥፋት
D. የወንጀለኛ መቅጫ ህግን ማጠናከር

**Answer:** B
While legal and institutional frameworks are important, creating attitudinal change across society is the most fundamental and sustainable measure to eradicate corruption.

**48.** አንድ ሰው መብቱን ሲጠይቅ ምን አሟልቶ መገኘት አለበት (1)

A. ✓ **ግዴታውን**
B. ድርሻውን
C. ፍላጎቱን
D. ቃልኪዳኑን

**Answer:** A
In civic education, rights and duties are inseparable; an individual must fulfill their civic responsibilities and duties (ግዴታውን) to legitimately claim and enjoy their rights.

**49.** በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገ መንግስት አንቀፅ 25 ስለምን ደንግጓል? (1)

A. የመደራጀት መብትን
B. የሴቶች መብትን
C. ፍትህ የማግኘት መብትን
D. ✓ **የዜጎች እኩልነት መብትን**

**Answer:** D
Article 25 of the FDRE Constitution explicitly guarantees the Right to Equality (የእኩልነት መብት), stating that all persons are equal before the law.

**50.** አንድ ታሪክ ትክክል ነው የሚባለው መቼ ነው? (1)

A. ፀሐፊው በራሱ ፍላጎት ላይ ተመርኩዞ ሲፃፍ
B. በመንግስት ባለስልጣናት ፍላጎት ሲፃፍ
C. ✓ **ትክክለኛ መረጃ ላይ ተመርኩዞ ሲፃፍ**
D. አንድን ብሄርን መሰረት አድርጎ ሲፃፍ

**Answer:** C
Historical accounts are considered accurate and objective when they are based on verified facts and reliable evidence (ትክክለኛ መረጃ), rather than bias or personal interest.

**51.** ዜጎች ፍትህን ለማስከበር ሲሉ መጠቀም የሌለባቸው ድርጊት የቱ ነው? (1)

A. ፍርድ ቤትን መጠቀም
B. ለፍርድ ቤት ይግባኝ መጠየቅ
C. ✓ **ጉልበት መጠቀም**
D. ባህላዊ የፍትህ አካላት

**Answer:** C
Citizens must use peaceful, legal, and constitutional institutions to seek justice; taking the law into one's own hands by using force (ጉልበት መጠቀም) is illegal.

**52.** በኢ.ፊ.ዴ.ሪ መንግስት ህግ አስፈፃሚ አካል ያልሆነው የቱ ነው? (1)

**A.** የጤና ሚኒስቴር
**B.** የመከላከያ ሚኒስቴር
**C.** ✓ **የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት**
**D.** የትምህርት ሚኒስቴር

**Answer:** C
The House of Peoples' Representatives (የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት) is the highest legislative body (ህግ አውጪ) of the federal government, not an executive body.

**53.** አዲሱ የሀገር ፍቅር ስሜት መገለጫዎች ከሆኑት መካከል አንዱ ነው (1)

**A.** በጦርነት ላይ መሳተፍ
**B.** ✓ **ጠንክሮ መማር**
**C.** የህይወት መስዋትነት ማድረግ
**D.** ተጋድሎ መፈፀም

**Answer:** B
Modern (new) patriotism is manifested through activities like working hard, learning diligently (ጠንክሮ መማር), and fighting poverty, whereas traditional patriotism focused mainly on military defense and warfare.

**54.** የሰው ልጅ የዕለት ተዕለት የአኗኗር ዘይቤን የሚገልፅ ነው (1)

**A.** ✓ **ባህል**
**B.** ሐይማኖት
**C.** እምነት
**D.** አመለካከት

**Answer:** A
Culture (ባህል) is defined as the total daily way of life, traditions, and practices of a society (የዕለት ተዕለት የአኗኗር ዘይቤ).

**55.** ከሚከተሉት መካከል ስለ ፌዴራል ህገ-መንግስት ትክክል ያልሆነው (1)

**A.** ሁለት ምክር ቤቶች አሉት
**B.** አስራ አንድ ምዕራፎች ይኖሩታ
**C.** 106 አንቀፆች አሉት
**D.** ✓ **የተዘጋጀው በ1989 ዓ.ም ነው**

**Answer:** D
The FDRE Constitution was adopted and ratified in 1987 E.C. (1994/1995 G.C.), not in 1989 E.C.; it consists of 11 chapters, 106 articles, and establishes two federal houses.

END OF THE MARKING KEY

Sit this paper online at temari.et/exam-prep/papers/grade-8-civics-2012-model.
More exam papers are at temari.et/exam-prep/papers.

Generated on Tikimt 2, 2019 E.C. (October 12, 2026 G.C.) · Temari.et